# ንገሩት ለዚያ ሰው

ዘመን አረጀና ፤ የማይሆነው ሆነ ፤ አምላክም ተቆጣ
በትር አያሻውም ፤ ፈጣሪ ፍጥረቱን ፤ ሲገስፅ ሲቀጣ
በመንደር በሰፈር ፤ የተሰባሰበ ፤ ውርጋጡን አመጣ
በደንቆሮ እሳቤ ፤ ከፍ ብሎ ሊታይ ፤ የሚሰራው ቢያጣ
በሰንደቃችን ላይ ፤ ይዘባበት ጀመር ፤ አጉል ተቀናጣ
ዕውነት ብትጨምት ፤ ዕብድና ዘበናይ ፤ ጭራሽ አይን ያወጣ ፡፡

በተዛባ ትርክት ፤ ግራ የተጋቡ ፤ ፈጣሪ ውኸንብር
ዝቅተኛ ስሜት ፤ ውስጡ የገነነበት ፤ የሆነበት ቸግር
ከራሱ የተጣላ ፤ ውስጡ ያልበቀለበት ፤ የናት ሐገር ፍቅር
ሐገሩን የሚያያት ፤ ባዕድ በለገሰው ፤ ሰባራ መነጥር
በተጋተው ተረት ፤ ማሰቢያው ጎርንቶ ፤ ከንቱ ሲቀባጥር
የቃኤል ድንጋዮች ፤ እሾህ አሜኬላ ፤ ወፍ የዘራው ፤ ቆንጥር
አይደለም ሰንደቋን ፤ ሐገሩን ለመናድ ፤ ይታያል ሲታትር ፡፡

የሰው ዘር መገኛ ፤ እናት ሐገራችን ፤ ኢትዮጵያዬ እማማ
ባለ ሶስት ቀለሙ ፤ ሰማይ የሚታየው ፤ የሐገራችን አርማ
ሲወርድ ሲዋረድ ፤ ጥንትም የነበረ ፤ እፁብ ድንቅ ፤ ወርቃማ
የምትውለበለብ ፤ በመላ ምድሪቱ ፤ ከፍ አርገን ፤ ከማማ
እንኳንስ የአዳም ልጅ ፤ ሳር ቅጠል የሚያውቃት ፤ የተሞላች ግርማ
የተሰጠችን ናት ፤ በሶስቱ ስላሴ ፤ በድንግል ታትማ ፡፡

የፃድቃን በረከት ፤ እማማ ኢትዮጵያ ፤ እናት ሐገራችን
አብ ወልድ ፤ መንፈስ ቅዱስ ፤ ፈጣሪ ያፀናት ፤ ሰንደቅ ዓላማችን
ታትሞ የሚኖር ፤ ሕብራዊ ቀለሟ ፤ ያለው በልባችን
ፍቅሯ ፤ ወደር የለሽ ፤ ለዘላለም ኗሪ ፤ በደም ባጥንታችን
ጠላት ከሚፈራው ፤ ከሚያርበደብደው ፤ ከጦር ከጋሻችን
ከናት ሐገር እኩል ፤ የምንሳሳላት ፤ እንዳይን ብሌናችን
የተጋመደ ነው ፤ የምንመካበት ፤ ሰንደቅ አላማችን ፡፡

ከአፅናፍ እስከ አፅናፍ ፤ እስላም ክርስቲያኑ ፤ በአንድነት ተነስቶ
ለምዬ ኢትዮጵያ ፤ ለናት ሐገሩ ክብር ፤ ለሰንደቋ ሞቶ
በዓለም መድረክ ላይ ፤ ከፍ ከፍ ፤ ያረጋት ፤ የምትታይ ጎልቶ
እንኳንስ ሀበሻ ፤ መላው አፍሪካዊ ፤ በሷ ተመክቶ
ቀድሞ የነበረውን ፤ ባረንጓዴ ቢጫ ፤ ቀይ ፤ ሕብር ተክቶ
የጥቁር ዘር ሁሉ ፤ ምስክር ይቆማል ፤ ለዕውነት አፉን ሞልቶ ፡፡

እኛን ከማይመስሉ ፤ ታሪካዊ ጠላት ፤ ዲሪቶ ሰብስቦ ፤ እየተሸከመ
አረባዊ ሰንደቅ ፤ በጥቁርና ነጭ ፤ አሊያም በግራር ፤ ሊተካ ያለመ
ሹምባሽና ባንዳ ፤ ደም የለበሰ ዐይኑ ፤ አረፋ እስኪደፍቅ ፤ እያጉረመረመ
አረንጓዴ ቢጫ ፤ ቀይ ሃር የለበሰ ፤ ለምን አየሁ ብሎ ፤ ወዶ ለታመመ
ለዚህ ካብ አይገባ ፤ ከናቱ ማሕፀን ፤ ቀድሞ የተረገመ
ንገሩት ለዚያ ሰው ፤ የሚለወጥ የለም ፤ አለቀ አከተመ ፡፡

ታዛቢው

February 22, 2020